ሐሳብን በነፃ መግለጽ መብት ነው

# ሩሕ

ሩሕ 1ኛ ዓመት ቁ. 02 ህዳር 1993



«የአሁኑ ረሀብ በአገራችን ታሪክ ትልቁ ነው...»
አቶ ሺመልስ አዱኛ




«ባለን መረጃ መሠረት 10,583 መምህራን ከስራቸው ተፈናቅለዋል ታስረዋል ተገድለዋል»
ኢመማ

ሄሊኮፕተሯን ኮረብታ ስር አሳርፎ የቀ.ኃ.ሥን አስከሬን ተሸክሞ ወረደ...

# አዲስ አበባን የኢየሩሳሌም ዕጣ ይጠብቃት ይሆን?

«ከባድመ ጀምሮ እስከ... በታሪክ ጥናት የኤርትራ አካል መሆኑን ደርሰንበታል»
(መለስ ዜናዊና አባይ ፀሐዬ)
በግዛው ብርሃን ዘደቡብ

# ቃለ - መጠይቅ

ኮ/ል ዓለሙ ቂጢሳ በ1907 ዓ.ም መጋቢ 5 ቀን በጅባትና ሜጫ አውራጃ በጀልዱ ተወለዱ:: በ1924 ዓ.ም በክብር ዘበኛነት ወታደርነት ተቀጥረው እስከ ማይጨው ወረራ ድረስ አገልግለዋል:: በሃምሳ አለቅነት ማዕረግ ከጠላት ጋር ተዋግተዋል:: ለጥቂት ጊዜ በንግድ ሥራ ቢቆዩም ተመልሰው ወደ ውትድርናው ዓለም ገብተው እስከ 1957 ዓ.ም ድረስ ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በኮሎኔልነት ማዕረግ በጡረታ ተገልለዋል::

ኮ/ል ዓለሙ ለ38 ዓመታት የመጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበርን በፕሬዝዳንትነት እየመሩ ነው:: በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ለሰባት ዓመታት ታስረዋል:: የመታሰራቸው መንስዔ የመጫና ቱለማ ማህበርን በማቋቋማቸው መንግሥትን ለመገልበጥ አሲራችኋል ተብለው ሲሆን፤ አብረዋቸው ከታሰሩት ሞት ከተፈረደባቸው ውስጥ አንዱ ተገኚል:: ዛሬ የ86 ዓመት የዕድሜውን ባለፀጋ ቢሆኑም ማህበራቸውን እየመሩ ነው:: ማህበራቸው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት «አዳማ» የኦሮሞ ርዕሰ ከተማ ነች ብሎ ሲወስን ውሳኔውን ተቃውሟል:: በዚህና በሌሎች ጉዳዮች ሰፊ-ቃለ ምልልስ አድርገናል:: ጊዜያቸውን ሰውተው ለሰጡት ቃለ ምልልስ በቅድሚያ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

ሩሕ:- የመጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር መቼ ተመሰረተ? ዋና 1ዓላማውስ ምንድን ነበር?


ኮ/ል ዓለሙ:- ማህበሩን ለመመስረት ያነሳሳን ምክንያት በ1953 ዓ.ም ጀ/ል መንግስቱ ንዋይ መንግስትን ለመገልበጥ አመጽ አስነስቶ ሳይሳካለት የመቅረቱ ጉዳይ ነው:: ይኸውም ምናልባት ወደፊት እንዲህ ያለ እገዳ ቢደገም የኦሮሞ ሕዝብ ራሱን ችሎ የመቋቋም ግዴታ ስላለበት አንድነቱን አጠናክሮ እንዲቆይ ለማድረግ ነው ማኅበሩ የተቋቋመው:: ቢሆንም የተቋቋምነው በልማት አስፈቅደን ነው:: በማኅበሩ ደንብ መሰረት ትምህርትን ለማስፋፋት፣ ኋላቀርነትን ለማስወገድና ረሀብና በሽታን ለማጥፋት፣ እንዲሁም ሌሎችን የልማት ሥራዎችንም ለመስራት ነው::

ሩሕ:- በደርግ ሥርዓት በማህበሩ ምክንያት የደረሰብዎት ችግር አለ? በምንስ ሙያ ነበር የሚተዳደሩት?

ኮ/ል ዓለሙ:- በደርግ ጊዜ አልታሰርኩም:: ቤንዚል ማደያ ስለነበረኝ በርሱ ስተዳደር ቆይቻለሁ::

ሩሕ:- በአሁኑ ወቅት የኦሮሚያ ክልል ገዥ ፓርቲ የሆነው ኦህዴድ የኦሮሞን ሕዝብ መብት አስጠብቂያለሁ ይላል:: በእርስዎና በማህበርዎ ዕምነት ይህ ሀቅ ነው ትላላችሁ?

ኮ/ል ዓለሙ:- እኔ የኦሮሚያ ክልል መንግስት ተቋቋመ የሚባለው ምኑም ሊገባኝ አልቻለም:: የማን ፓርቲ እንደሆነ ማንን እንደሚደግፍም አይገባኝም:: እንደ ዕውነቱ ከሆነ አሁን የኦሮሞ አስተዳደር የሆኑት ሁሉ ቀድሞ በውትድርና ከደርግ ጋር የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያደሙ የቆዩ ናቸው:: ትግራይም ላይ ለመዋጋት ነው የሄዱት እንጂ ኦሮሞን ነፃ ለማውጣት እንዳልሄዱ ማንም ሰው ያውቃል:: ለዚህ ነው የሄዱት ብዬ ብናገር እንኳን ሰው አይቀበለኝም:: እዛ ሄደው ተማረኩ:: ከተማረኩት ውስጥ ከፍተኛ ማዕረግም ዝቅተኛ ማዕረግ ያላቸውም ነበሩ:: ከተማረኩት ባለ ከፍተኛ ማዕረጎቹ ይልቅ ዝቅተኛ ማዕረግ ያለው ኃላፊ ሆኖ ኦሮሚያን እንዲያስተዳድር አቶ ኩማ ተወክሎ አየሁት:: ጀነራሎችም ኮሎኔሎቹም ተማርከዋል:: ምን ልዩ ነገር እንደሰጠ ባላውቅም እኔ እንደማስበው ኦህዴድ መቶ በመቶ የኢህአዴግ ደጋፊ ፓርቲ እንጂ የኦሮሞ ፓርቲ ነኝ ብሎ ኦሮሞን ለመግዛት ካልሆነ ለኦሮሞ መብት የቆመ ነው ብዬ አልቀበለውም:: መቀበልም አይገባም:: ማንም ሰው አይቀበለውም:: ኦሮሞ እስካሁን ድረስ እገሌ ያስተዳድረን ብሎ የመረጠው ሰው የለም:: አቶ ኩማም ቢሆን የተሾመው በኢህአዴግ ነው:: ዶ/ር ነጋሶም የተሾሙት በእነሱ እንጂ ለኦሮሞ ሕዝብ መብት ተሰጥቶ በመብቱ ፕሬዝዳንት እናንተ ምረጡ ተብሎ አይደለም:: የኦሮሞ ሕዝብ ዶ/ር ነጋሶንም አልመረጠውም:: ሁለቱም



ኮ/ል ዓለሙ ቂጢሳ

በኢህአዴግ ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ እንደተሾሙ ነው የምቆጥረው::

ሩሕ:- አንዳንድ ወገኖች የአሁኑ ሥርዓት ካለፈው አስተዳደር የተሻለ ነው ይላሉ:: እርስዎ በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድነው?

ኮ/ል ዓለሙ:- ሁሉንም ጥሩ አድርጌ አውቃለሁ:: አንድ ተረት ነው ልነግርህ የምፈልገው:: ይሄም ተረት «ዝንጀሮ በርበሬ ላይ ተቀመጠና በርበሬው መቀመጫውን አቃጠለው:: በኋላ ለጦጣ እባክሽ መቀመጫዬ ተቃጥሏልና ምን ይሻለኛል ብሎ ቢያማክራት እዚያ ጥቁር ቅጠል ላይ መቀመጫህን ብታሽ ይበርድልሃል አለችው::» ጥቁሩ ቅጠል ሳማ ነበር:: ምክሩዋን ተቀብሎ ሄዶ ሲያሽ የባሰውን አቃጠለው:: ስለዚህ በእኔ ዕምነት እየባሰ ከሚሔድ በስተቀር አስተዳደሩ ከድሮው የአሁኑ የተሻለ ነው ብዬ አልናገርም:: የድሮውንም እቃወም ነበር:: የአሁኑ ደግሞ እንዳየሁት የባሰ ነው:: የአሁኑ አስተዳደር የባሰ ነው ያልኩበት ምክንያት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ሰው የሰራውን ቤት አልተወረሰም:: አልተገፈፈም:: የገዛውን እርስትም ይተዳደርበታል:: ንብረቱ ሙሉ በሙሉ የራሱ ነው:: በደርግ ጊዜ ተወረሰ:: ኢህአዴግ ደግሞ ቢመጣ የደርግን አጥንቶ የሕዝቡን ንብረት ወስዶ ባለቤት ሆኖ ሕዝቡን እንደ ጭሰኛ፣ ከአባት ቅድመ አያቱ ከዘሩ ከትውልዱ የተወለደበትን እንደ ባይተዋር፣ አደዋን ማይጨውን ለእገሌ ሰጠን እያሉ የሰው እርስት እየሸጡ እየነገዱ ስለሄዱ ይብሳል ያልኩበት ምክንያት ይሔ ነው::

ሩሕ:- ከጥቂት ወራት በፊት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት የክልሉ ዋና ከተማ አዳማ ናት ሲል አፅድቋል:: ማህበራችሁ ለምንድነው ይሄን ውሳኔ የተቃወመው?

ኮ/ል ዓለሙ:- በመጀመሪያ አንድ ከተማ ሲመሰረት የሕዝቡ ፍላጎትና የሕዝቡ ዓላማ ይዞ መሆን አለበት እንጂ እንዲሁ ከሕዝቡ ፍላጎት ውጪ ማንም ሰው ከተማ መከተም አይችልም:: የሕዝቡ ዋና ከተማ አዲስ አበባ እየሆነና ከተማው የኦሮሞ እርስት መሆኑ

እየታወቀ አዲስ አበባን ለቆ አዳማ የሚሔድበት አይነተኛ ምክንያት ሊኖረው አይችልም:: ይሄን ማድረጉ በመሰረቱ ከባድ ስህተት ነው:: ደግሞም አዳማ መላውን ኦሮሞ ምሥራቁንና ምዕራቡን ደቡቡንና ሰሜኑን አስተባብሮ የሚያስተዳድር ቦታ አይደለም:: አማካይ አገር ፊንፊኔ ሲሆን መሬቱ የኦሮሞ ነው፣ ከተማውም የኦሮሞ ነው:: ሌላ ስንት ብዙ የሚሰራ ስራ እያለ ከዚህ በመሔድ አዲስ ከተማ ለመሰየም ገንዘብን ማባከንና የሕዝብንም ሀሳብ ለመበተን ይሄ መደረጉ ከስህተትም ስህተት ነው:: ለዚህም ነው መጫና ቱለማ ውሳኔውን የሚቃወመው:: ይሄ ብቻ ሳይሆን አዳማ በመሬት አቀማመጥ፣ በውሃ፣ በክሊኒክ፣ ለከተማነት ምንም ምቾት የለውም:: እንኳንስ የኦሮሞ ከተማ ሆኖ ይሄ ሁሉ ሕዝብ የወለጋው፣ የጅማው፣ የኢሊባቡር ሕዝብ ይህን ሁሉ ከተማ አልፎ ለአቤቱታ ለይግባኝ እዛ እንዲሄድ መደረጉ ደግሞ ከፍተኛ ሸክም ነው:: ምቾት የሌለው አቋም ነው:: ለሕዝቡም አያመችም ለከተማነትም አይሆንም:: አዳማ እንኳን ይሄ ሁሉ ሰው ተጨምሮ ባለበት ሁኔታ እንኳን ብዙ ያስቸግራል:: አንድ ሰው ብቻውን ሕዝብ ያልመረጠው ወስንልኝ ብሎ ስልጣን ያልሰጠው በሌላ ሰው የተሾመ ሰው የኦሮሞ ከተማ አዳማ ነው ብሎ የወሰነ ሰው በዕውነቱ ኦሮሞ በምድር ላይ እንደሌለ የቆጠረ ካልሆነ በስተቀር የኦሮሞን ሕዝብ ባይንቀው ኖሮ ይሄንን እርምጃ ምክር ሳያደርግ ባልወሰነ ነበር:: ምክር ቤቱም ይሄንን የተቀበለው አይመስለኝም:: አልተባበረበትም:: ቢተባበርበትም እርስ በርሳቸው ተመራረጡ እንጂ በሙሉ ሕዝብ ድምፅ ያልተመረጡ ስለሆነ ይሄ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም:: ሕዝቡ ዛሬም ከእኛ ጋር ኡኡ የሚል እንጂ አልተቀበለውም:: ደግሞ ይሄ ለውድቀት እንጂ ለጥቅም የመጣ ስላልሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ መቶ በመቶ የበለጠ ስለሆነ ነው የአዳማን ከተማነት የተቃወምንበት አይነተኛ ምክንያት:: ስለዚህም ማህበራችን ተቃውሞውን ለምክር ቤቱ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ፣ ኦሮሞን ወክዬያለሁ ለሚለውና ይሄን ከተማ ለሰየመው ለአቶ ኩማም ልከናል:: ከአገር ውጭም ለዓለም አስተላልፈናል:: ለተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አሰራጭተናል:: ውሳኔው የሕዝቡን ፍላጎት የማይወክል ነው:: ለምን? ዋና ከተማችን ፊንፊኔ የራሳችን ነው:: ከተማው ሳያንስ ለሰው ለቀን የምንሄድበት ምክንያት የለም ብለን ለሁሉም አስታላልፈናል::

<u>ሩሕ</u>:- ውሳኔውን በመቃወማችሁ የደረሰባችሁ ችግር አለ?

<u>ኮ/ል ዓለሙ:-</u> በዚህ ሳቢያ ተብሎ ቀጥታ የደረሰብን ነገር የለም:: ውስጥ ውስጡን እንጂ በጉልህ የተነገረ ነገር የለም:: ነገር ግን ውሳኔውን በተመለከተ አንድ ስብሰባ አድርገን በነበረበት ጊዜ የድርጅታችን ምክትል ፕሬዚዳንት የሆነው ዶ/ር ሞጋ ፍሪሳ ይሄንን ነገር አብራርቶ ሳለ ወር ሳይቆይ ሌላ ምክንያት ፈልገው አሰሩት:: ሆኖም ያሰሩት በማስረጃ ያልተደገፈ ስለሆነ ጉዳዩ ውድቅ ሆኗል:: በመጫና ቱለማ ማህበር ጉዳይ አባሎቻችን የሆኑ በርካታ ሰዎች ታስረዋል:: የታሰሩትን አባሎቻችንን ቆጥሬ አልጨርስልህም አዲስ አበባ እንኳን ከአባሎቻችን 22 ሰው ወህኒ ቤት በእስር ላይ ይገኛሉ:: ከፍተኛ የሕግ አንቀጽ ጠቅሰውባቸው የዋስ መብታቸውን ክልክለዋል:: ማስረጃ አልቀረበም ግን 3 ዓመት ታስረዋል:: ኦነግን ትደግፋላችሁ እያሉ ምክንያት እየፈጠሩ አባሎቻችንን ያስራሉ:: የአዳማን ውሳኔ በመቃወም ተማሪዎችም ታስረው ተፈተዋል:: አቶ ኩማ ጋ ለአቤቱታ ሲሄዱ ፖሊሶች ናቸው ይዘው ያሰሯቸው::

<u>ሩሕ</u>:- በሥልጣን ላይ ያለው ሥርዓት በሕዝብ ተመርጫለሁ ይላል:: ማህበራችሁ በኢትዮጵያ በሕዝብ የተመረጠ ስርዓት አለ ብሎ ያምናል?

<u>ኮ/ል ዓለሙ</u>:- ደርግ አፄ ኃይለ ሥላሴን ከመንበራቸው ካነሳበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ሥርዓት ሁሉ አቤቱታ የማይሰማበት፣ በብዙ መንገድ ዳኝነት የማይታይበት፣ የበላይ የሆነ ሰው አቤቱታ የቀረበለት እንደሆን የማይቀበልበት ጊዜ ነው:: ለምሣሌ ጠ/ሚ/ር ቢሮ ለማነጋገር ብፈልግ ሰማይን እንደማግኘት ያህል ነው:: አንድ ባለሥልጣን አግኝቶ ጉዳዬ ይሄ ነው ብሎ ለማብራራት የባለስልጣኑ ፍላጎት

> *...አማራም ቢሆን ከተማውን አዲስ አበባ ብሎ ይሰይም እንጂ በኦሮሞ መሬት ላይ ነው የሰየመው:: የአሁኑ ገዢ ትግሬም ቢሆን በኦሮሞ መሬት ላይ ነው ስልጣኑን የያዘው::...*

ካልተጨመረበት በስተቀር በሥርዓት መብት አለኝ ብሎ ሄዶ ለማግኘት በጣም ችግር አለ:: አሁን እንደማየው አንድ ሰው ምን ጉዳይ አለህ ተብሎ ተጠይቆ በፀሐፊ ነው የሚመለሰው::

<u>ሩሕ</u>:- እናንተ እንደምትሉት የኦሮሚያ ዋና ከተማ ፊንፊኔ (አዲስ አበባ) ብትሆን የሌሎች ክልል ተወላጆች ዕጣ ምን ይሆን ነበር?

<u>ኮ/ል ዓለሙ</u>:- ፊንፊኔ ሁሉንም ይችላል ባይ ነን እንጂ ሌሎቹ ይውጡ አንልም:: ግን ማንም ሰው ቤቱን ለእንግዳ ለቆ አይሄድም:: እዚህ ያሉት ሁሉም እንግዶች ናቸው:: አማራም ቢሆን ከተማውን አዲስ አበባ ብሎ ይሰይም እንጂ በኦሮሞ መሬት ላይ ነው የሰየመው:: የአሁኑ ገዢ ትግሬም ቢሆን በኦሮሞ መሬት ላይ ነው ስልጣኑን የያዘው:: ፈረንጆቹም አረቦቹም ማንኛቸውም መንገደኛ ሁሉ በኦሮሞ መሬት ላይ ነው እዚህ ያሉት:: ሁሉም አብሮ እንደኖረ ይኑር ይቀጥል እንጂ እኛ እገሌ ይውጣ እኛ እንያዝ አላልንም እስካሁን:: ወደፊትም ይሄን አንልም በግድ ተለያዩ ካላሉን በስተቀር:: አንድ ተረት አለ:: በድሮ ዘመን ዘመድ ወደ ዘመዱ ይግባ በተባለ ጊዜ ሰፌድ ወደ ስንደዶ ገባች ይባላል:: በግድ ተለያዩ በሚለው ሕግ ሕዝብ እንለያይ ብሎ ካልወሰነ በስተቀር የመጫና ቱለማ ማህበር ሕዝቡ ካለበት እንዲሰደድ ውጣ ግባ የሚል ዓላማም የለውም:: በማህበሩ ደንብ ውስጥም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ በአባልነት ይቀበላል ይላልና ማህበራችን የዚህ ዓላማ የለውም::

<u>ሩሕ</u>:- የመጫና ቱለማ ማህበር ዓላማ ኢትዮጵያውያንን የሚያቅፍ ጭምር ነው ብለውኛል:: ግን ማህበሩ ብዙ ጊዜ ሲከራከር የሚሰማው ስለ ኦሮሞ ብሔር ብቻ ነው:: ይሄ ማህበሩን ብሔርተኛ አያሰኘውም?

<u>ኮ/ል ዓለሙ</u>:- ብሔርተኛ አያሰኝም:: ሌላው ራሱን ገልሎ ስለተቀመጠ የግድ እኛም ለራሳችን ክልል ነው የምንከራከረው:: አማራውም አማራ አለው:: ለምሳሌ አብረን የምንኖረው ጎረቤታችን የሆነውን ደብረብርሃን ባህር ዳር ወስዶታል:: ስለዚህ እኛም ኦሮሞን ካለበት ቦታ ሰብስበን መብታችንን ለማስከበር ኦሮሞነታችንን ለማሳወቅ ከመጣር ወደኋላ የምንልበት ምክንያት የለም:: ይሄንን ያደረገው ግን የአሁኑ አስተዳደር መንግስት ነው:: ኦሮሞ የፌደራልን አቋም አይጠላም:: በአፄ ሚኒሊክም ጊዜ ሁለት ኦሮሞዎች ፌደራሎች ነበሩ:: ጅማና ወለጋ ማለት ነው:: ሌሎቹ ተዋጋን ብለው ከፌደራል መብት ወሰዱብን እንጂ ፌደራል ነበር መሆን ያለበት:: የፌደራል ስርዓት አንጠላም፤ አንወዳለን:: ግን ወገንን፣ ጎሳን፣ አንተ አማራ፣ አንተ ሻንቅላ ነህ፣ አንተ ትግሬ፣ አንተ ጎጃሜ፣ አንተ ጎንደሬ ነህ፣ ብለን አባረን አናውቅም:: አቅፈን ነው ያለነው:: ተዋልደናል፣ ተጋብተናል፣ ግን ባለቤቱ እሄዳለሁ ካለ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ሰፌድ ወደ ስንደዶ ገባች እንደሚባለው በፍላጎቱ ወደ አገሩ ቢገባ አንቃወምም:: ከዚህ ውጭ እኛ ሂዱ አንልም:: አብረን ነው የምንኖረው:: አብረን ነው የኖርነው መለያየቱ መጥፎ ነው:: አብሮ መኖር ጠቀሜታ አለው::

<u>ሩሕ</u>:- አዳማ የኦሮሞ ዋና ከተማ ለመሆን ምን ይጎድላታል ትላላችሁ? ከፊንፊኔስ ሌላ ለከተማነት የምታስቀምጡት ሌላ አማራጭ የለም?

<u>ኮ/ል ዓለሙ</u>:- በተለይ ይሄ ጉዳይ ሲነሳ እኔ በግሌ የማስበው ጠቅላላ ኦሮሚያን ለአንድ ሰው ሰጥቶ ተሸከም እንደማለት ነው:: እንደማየው ኦሮሚያን እናስተዳድራለን የሚሉት ሰዎች አስተባብሮ ለመግዛት ከብዷቸዋል:: ከአቅማቸው በላይ ሆኖ ነው የማየው:: አላወቁትም:: ኩንታል መሸከም ይቀላል ሰውን ማስተዳደር ቀላል አይደለም:: ችሎታን፣ ዕድሜን፣ ልምድን ይጠይቃል:: ማስተዳደር አልቻሉም:: ከብዷቸዋል:: ቢከፋፈልና ለምሳሌ በአምቦ በኩል ከፊንፊኔ ጀምሮ እስከ ወለጋ ድረስ፣ በጅማ መንገድ ደግሞ ከፊንፊኔ እስከ ኢሉባቡር ድረስ፣ በምሥራቅ ከፊንፊኔ አንስቶ አዳማን ጨምሮ

እስከ ሐረርጌ፣ አርሲና ነገሌ ቦረናም ራሱን ችሎ፣ ወሎም እራሱን ችሎ አስተዳደር ተደርጎለት አንድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ፊንፊኔ ላይ ተቋቁሞ ቢያስተዳድር የሚቀል ይመስለኛል:: በዚህም ኦሮሚያን በሰባት ከፍሎ ሰባት ዋና አስተዳዳሪዎች ይኖሩታል፣ ከተማውም ባለበት ቦታ ይስፋፋል:: የፊንፊኔውም አንድ ይዞታ ይኖረዋል:: ሰላሌን፣ አዲስ አበባ ዙሪያውን ይዞ አንድ ሰው የፊንፊኔ አስተዳዳሪ ይሆናል:: የሁሉም ማዕከላዊ በምትሆነው ፊንፊኔ ላይ ከሁሉም የተውጣጡ ሕዝብ የመረጣቸው ባለሥልጣኖች እዚህ ሆነው ቢያስተዳድሩ በእኔ ግምት ጥሩ ይሆናል ብዬ ነው የማስበው:: ይህ ሁሉ የእኔ ግምት ነው እንጂ መጫና ቱለማ አስተዳደር ውስጥ ገብቶ እንደዚህ ይሁን አላለም:: ግን ይህ ካልሆነ አሁን እንደሚታየው ሽክሙ እጅግ አድርጎ አቶ ኩማን ውጦታል ይሄን ሁሉ ማስተዳደር አይቻለውም:: ዕድሜውም አይችልም፣ ችሎታውም አይፈቅድለትም:: አቅምም የለውም ከመጠን በላይ ነው ያሸከሙት:: በዝቶበታል:: ስለዚህ ይከፋፈልና ለአስተዳደር አመቺ ይሁን ነው የእኔ ዓላማ::

ለኦሮሚያ ዋና ከተማነት ግን ከፊንፊኔ ውጭ ይሄ ይሁን የምለው የለኝም:: ፊንፊኔ እንደነበር አሁንም መሆን አለበት:: ዋና የኦሮሚያ እምብርት ነው:: የፌደራልም መንግሥት ይኑርበት:: ሌላም ሰው መጥቶ ቢኖርበት እኛ አንቃወምም:: ኦሮሞ ይልቀቁልን ብሎ አይቃወምም:: የኦሮሞ ህዝብ በዚህ ከተማ መብቱን መጠቀም አለበት:: ይሄ ከተማ በኦሮሞ ስር ሆኖ እንደ አንድ ክልል ከተማውን እዚህ ሆኖ ማስተዳደር አለበት:: አዲስ አበባ የኦሮሞ መሬት የኦሮሞ ከተማ ነው:: መብቱም ነው:: ይሄንን መብቱን መልቀቅ አይገባውም::

ሩሕ:- ፊንፊኔ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ብትሆን የሥራ ቋንቋ ምን ይሆናል? የሁሉም መቀመጫ ቢሆን አንቃወምም ከማለትዎ ጋር አያይዘው ቢያዩት?

ኮ/ል ዓለሙ:- የኦሮሚያ መስሪያ ቤት በመረጠው ቋንቋ ይጠቀም:: ሌሎቹ ፌዴራል መንግሥቱ በመረጠው ቋንቋ መጠቀም ይችላሉ:: ስለዚህ ይሄ የሚያጣላ አይመስለኝም:: አሁንም ሕዝቡ በይበልጥ የሚጠቀመው በአማርኛ ቋንቋ ነው:: እኔም የማነበውና የማወራው አማርኛ ቋንቋ ነው:: ሌላኛውን ቋንቋ አላውቅም:: የኦሮሚያ ሕዝብ ቋንቋውን ከመረጠ በራሱ ቋንቋ የራሱን አስተዳደር ይመራል:: አማራም በአማርኛው ፌደራሉም በመረጠው ይመራል::

ሩሕ:- የኦሮሚያ ዋና ከተማ አዳማ ነች ተብሎ ተወስኗል:: ይህ ውሳኔ ዘላቂ ከሆነ የማህበራችሁ ቀጣዩ እርምጃ ምን ይሆናል?

ኮ/ል ዓለሙ:- በሰላማዊ ሰልፍ እንቃወማለን:: ለዓለም ሁሉ እናስታውቃለ
ን:: አሁንም በማሳወቅ ላይ ነን ያለነው:: ይሄን አልፈው ከሔዱ በሕጋዊ መንገድ ከመቃወም ውጭ በጉልበት የምናደርገው ነገር የለም::

ሩሕ:- የኦሮሚያ ዋና ከተማ ፊንፊኔ ናት የምትሉት ከምን ተነስታችሁ ነው የታሪክ ማስረጃ አለ?

ኮ/ል ዓለሙ:- አለ:: ፊንፊኔ ከተማ የኦሮሞ ከተማ የኦሮሞ መሬት ነው:: እርስቱ ነው:: ኦሮሞ የመረጠው ቦታ ላይ የመሆን መብቱ እያለው መብቱን ለቆ ለምንድነው ወደ ቆላ የሚሄድበት? ታሪክ አለው:: የጉለሌ መሬት የቱፋ ሙና መሬት ነው:: በዚህም በዚያም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድም ጣልቃ የለም ሁሉም የኦሮሞ መሬት ነው:: ስለዚህ ይሄን ጠቅሰን ነው ርስታችንን ለቀን አንሄድም የምንለው:: እርስታችንን በሌላ መልክ ብንነቀል በአስተዳደር እንኳን መነቀል አይገባንም ባይ ነን:: ድሮ የአዲስ አበባ መጠሪያ በሙሉ በኦሮሚኛ ነው:: ምሳሌ የምንሊክ አደባባይ ቢርቢሳ ጎሮ ነበር የሚባለው፤ ደበሶ በኋላ ተለውጦ ቸርቸል ጎዳና ተብሏል:: ጨፌ አራራ ዛሬ ቤተ መንግሥቱና አካባቢው ነው:: ፊንፊኔ ፍልውሃው ነው:: ሁሉም የራሱ ስም የራሱ ታሪክ አለው::

ሩሕ:- በሽግግር መንግሥቱ ወቅት የተወሰኑ የብሄሩ አባላት በሰልፍ ወጥተው የአፄ ሚኒሊክ ሐውልት ይፍረስ ብለው ጠይቀው ነበር:: በዚያ ወቅት የመጫና ቱለማ ማህበር ተሳትፎ ነበረው?

---

*ሕዝቡ ተገናኝቶ የሚበጀውን መክሮ ከዚህ እዚህ ይሻለናል ቢባል እኮ ሱማሌንም፣ ኤርትራንም፣ ጅቡቲንም ማምጣት ይቻላል::*

---

ኮ/ል ዓለሙ:- አልተሳተፈም እንደውም አልሞከረም:: መጫና ቱለማ እንደዚህ ያለው ጣጣ ውስጥም አልገባም፣ ይፍረስም አላለም:: ታሪክ ያፍርሰው እንጂ እኛ ለምን እናፈርሰዋለን? የአንድን ሰው ሐውልት ሥራውና ታሪኩ ነው የሚያፈርሰው:: ታሪክ ሲያፈርሰው ራሱ አውቆ ይፈርሳል:: የማንም ሐውልት ደግሞ ታሪክ ነው የሚያኖረው:: ሰው ጥሩ ከሰራ ታሪኩ ያኖረዋል:: ሐውልቱም ቢፈርስ እንኳ ስሙ በጥሩ እየተጠራ ይኖራል:: መጥፎ የሰራውን ሰው ደግሞ ታሪክ ሲያወግዘው ይኖራል:: ማንም ሰው በዚህ ዓለም ላይ ስልጣን ይዞ ዕድሜ ልኩን አይኖርም:: ታሪኩ ነው የሚኖረው:: መጥፎም የሰራ ደግሞ በመጥፎ በታሪክ ሲጠራ ይኖራል::

ሩሕ:- የኦሮሞ ሕዝብ ቀደም ሲል ከነበሩት ሥርዓቶች የተሻለ አሁን መብት አግኝቷል ማንነቱ ታውቋል የሚሉ ወገኖች አሉ:: ማህበራችሁ በዚህ አስተያየት ይስማማል?

መልስ:- ፌደራል ይሁን ተብሎ መሰየሙ፣ የራሱን አስተዳደር ይቻል በመባሉ አንድ ውጤታማ መንገድ ነው:: ይሄንን ኦሮሞ አይጠላም:: ፌደራል ሆኖ ከሌላው ጋር አብሮ መኖሩንም አይጠላም:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ ለየብቻ ሆና ትጥፋ ሳይባል እያንዳንዱ በፌደራል ሆኖ በፌደራል ተገናኝቶ በጋራ አስተዳዳሪውን መርጦ በጋራ ስልጣን በአንድነት ባወጡት ሕግ አብሮ መተዳደርና የራሳቸውን ይዞታ በፌደራል ማስተዳደርን የኦሮሞ ህዝብ ይወዳል:: አይጠላም:: ነገር ግን ገባር ሆኖ እንደድሮው እኔ ነኝ የማውቅልህ፣ እኔ ነኝ እንደዚህ የማደርግልህ ተብሎ ያለ መብቱ በከፍተኛ ስልጣኑ ሰውን አንቆ ማስተዳደር ጥሩ አይደለም:: ታሪክንም ያበላሻል:: ይህ በደርግና በሌሎቹም ታይቷል:: እየተወቀሱ
በት ነው ዛሬም ቢሆን ትላንትም::

ሩሕ፣ ማህበራችሁ የልማት ማህበር ነው ብለውኛል:: የምታነሷቸው ጥያቄዎች ግን በፖለቲካ ድርጅት አይን አያሳያችሁም?

ኮ/ል ዓለሙ:- ይሄ ፖለቲካ አይደለም:: የመብት ጉዳይ ነው:: ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት የለውም:: የእኛ ማህበር ስለመብት ነው የሚከራከረው:: ማህበራችን ማንም ኢትዮጵያ ፖለቲከኛ ቢሆንም በኢትዮጵያዊነቱ መብት ስላለው በአባልነት ማህበራችን ያቅፈዋል:: የፖለቲካም ሰው የሚደግፈውን ፖለቲካ መደገፍ ይችላል:: እኛም ፖለቲካ ውስጥ አልገባንም ነገር ግን የኦሮሞ መብት መሆን ያለበት መመስረት ያለበት በዚህ አቅጣጫ ነው ብሎ የሚያምን ማህበር ነው:: የፖለቲካ መብትም ቢሆን ከዚህ ውስጥ ወጥቶ መወዳደር አለበት እንጂ የኦሮሞን ሕዝብ መብት ጥሎ ብቻውን ትከሻውን አሳብጦ እኔ የኦሮሞ ገዥ ነኝ ብሎ ቢመጣብን ይሄን እንቃወማለ
ን:: መጫና ቱለማ የሕዝብን መብትና ግዴታዎችን የሚያከብርና ስለሁለቱም የሚከራከር ነው::

ሩሕ:- የመጫና ቱለማ ማህበር በልማት መስክ እስካሁን ምን ምን ተግባራትን አከናውኗል?

ኮ/ል ዓለሙ:- አሁን በኢትዮጵያ በአስተዳደርም ሆነ በሚኒስትር ደረጃ ያሉት ኦሮሞዎች በሙሉ መጫና ቱለማ ከተቋቋመ ወዲህ በምክር ለበስ መብቱን አውቆ ተምሮ ስልጣን እንዲይዝ ያደረገ ነው:: በስንት ቦታ በተለያዩ አቅጣጫዎች መንገድ ቀይሰን በሥራ ላይ ውሏል:: ደርግም ቢከፋም በተግባር አውሎታል:: ልጆቹ እንዲማሩ ምክር የሰጠነው ሕዝብ በምክራችን ተጠቅሞ ልጆቹን ለከፍተኛ ደረጃ አድርሷል:: ድሮ መጫና ቱለማ ሲቋቋም የኦሮሞ ልጆች ከመቶ አንዱ እንኳን በዩንቨርስቲ የሉም ነበር:: ዛሬ በየዓመቱ በሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች ከየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው ይወጣሉ:: ይሄ የመጫና ቱለማ የሥራ ፍሬ ነው:: እኔም በግሌ በአገሬ ላይ ከአባቴ እርስት ቆርሼ፣ ትምህርት ቤት አስተባብሬ ሰርቻለሁ:: ከዚያ ት/ቤት ዛሬ ዶክተሮች፣ መሐንዲሶች፣ ሌሎችም ባለሙያዎች ወጥተው በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ይገኛሉ:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ከአባቴ ጀምረን ተዋግተናል:: ወላጆቼ በአድዋ ጦርነት ዘምተዋል:: አባቴ በሰገሌና ጦርነት በማይጨው ዘምቶ ለአገሩ ተዋግቷል:: ከዚያ በኋላ ነው የሞተው:: እኔም ብሆን ማይጨው ዘምቻለሁ:: እስካሁን ድረስ


(ወደ ገጽ 14 ዞሯል)

(ከገጽ 9 የዞረ)

በኢትዮጵያ ላይ የሚመጣውን አደጋ ለመከላከል መስዋዕት እየሆንን እያገለገልን ነው:: ይሄ በኢትዮጵያዊነታችንም በኦሮሞነታችንም ለአገራችን መስዋዕት ሆነን ያቆየነው ነው:: መጫና ቱለማ ያደረገውን ልቆጥርልህ አልችልም:: በሰላሌ፣ በሜታ ሮቢ፣ በአደአ በርጋ፣ በአርሲ፣ በአምቦ፣ በወላጋና በሌሎች ቦታዎች ት/ቤት እስከ ወረዳ ደረጃ ድረስ እንዲቋቋም ያደረግነው ማህበሩ ከተቋቋመ ወዲህ ነው::

ሩሕ:- መጫና ቱለማ ማህበር የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሳይነጣጠል በፌደራል ይኖራል ብሎ ነው የሚያምነው?

ኮ/ል ዓለሙ:- ፌደራልነቱን ያምናል:: ኢትዮጵያዊነቱንም ያምናል:: አብሮ መኖር ነው



የለመድነው:: ለምንድነው የምንነጣጠለው? ለየራስ የምሆንበት ምክንያት የለም:: ይህንን ሕግ እዚህ ውስጥ ወንከፍ አድርገው የጣሉት በጎሳ ወደየራሳቸው ለመቀላቀል የፈለጉት ሰዎች ናቸው እንጂ ይሄ ሕግ ከኦሮሞ ሕዝብ የወጣ ሕግ አይደለም:: ግን ኦሮሞን አይጎዳም:: እነሱን ነው መልሶ የሚጎዳው:: ኦሮሞ ሰውም ቢሄድበት ግዴለውም:: ራሱን የቻለ መሬት፣ ራሱን የቻለ አገር አለው:: አብሮም ለመኖር ደግሞ ተጋብቷል፣ ተዋልዷል፣ የሚጠላ አይደለም:: ግን የኦሮሞ ብሔራዊ መብት መከበር አለበት የሚል ምርጫ ላይ ተመስርቶ ነው የሚከራከረው:: ብሔራዊ መብቱ ምንድነው? ድሮ አርሶ ሁለት እጁን ለባላባት ይሰጥ ነበር:: የተማረው ስራ አያገኝም:: ለእነሱ ባሪያ ነው ሥራ የሚሰጠው:: ይሄ መሆን የለበትም:: ሥራ በአገር ላይ ካለ ተወዳድሮ ነው መያዝ ያለበት:: ይህን መብቱ ነው ይላል:: የመጫና ቱለማ ማህበር መነሻም ይሄው ነው:: እሱ እየሰራ ሌላውን የሚያበላበት ምክንያት የለም:: መብቱ መከበር አለበት:: በአገሩ ላይ ተወዳድሮ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ቦታ ማግኘት መብቱ ነው::

ሩሕ:- በኦሮሚያ ክልል ያለው ገዢ ፓርቲ የኦሮሞ ሕዝብ የሚገባውን ሥልጣን አግኝቷል ይላሉ:: ማህበራችሁ ይህንን አስተያየት ይጋራል?

ኮ/ል ዓለሙ:- በፌደራል ሕግ እኮ ሰው ሰውን አይሾምም:: ሕዝብ ነው ያስተዳድረኛል ብሎ የሚሾመው:: የኦህዴድ ባለሥልጣኖች የፈለጉትን ይሾማሉ የፈለጉትን ይሽራሉ:: ባለፈው ምርጫ ሕዝብ የመረጠውን እንኳን አርባ ሃምሳውን ነው ያገዱት:: ሕዝብ ነው የማገድ መብት ያለው:: አንድ አስተዳዳሪ የሆነ ሰው ወንጀል ቢሰራ በወንጀሉ ይከሰዋል:: ፍ/ቤት ያቀርባል:: ከሥራ ከማገዱ በፊት ያ ወንጀለኛ ጥፋተኛ ከሆነና ከተፈረደበት ለሕዝብ እናንተ የመረጣችሁት ሰው ጥፋት ስለሰራ ሌላ ምረጡ ብሎ ሌላ ያስመርጣል እንጂ ስራውን አስቁሞ ሌላ የፈለገውን ሰው ማድረግ የለበትም:: ይሄ አሁን ያለው አስተዳደር አይደለም:: የመሳሪያ አስተዳደር እንጂ የሰላማዊ አስተዳደር አይደለም:: አሁን ያለ ሥልጣን በመሳሪያ አፈ ሙዝ እንደፈለገ የሚነዳ ነው:: ማንም ባለሥልጣን በሕጋዊ መንገድ ሥራውን ሰርቷል ብዬ አላምንም:: የጉልበት ስራ ነው ያለው:: ደካማ ይገብራል ጉልበት ያለው ይዋጋል:: ይጣላል:: ይኸውና እርስ በርሳቸው ይጣላሉ:: ያለው መንግስት በኢትዮጵያ የሚያምን ከሆነ ለምንድነው ኤርትራን የለቀቀው? ለምንድነው ህዝበ ውሳኔ የምሰጠው? ለሌላው እንዲያመች ብሎ ነው ኢህአዴግ ይህን ያደረገው:: እኔ ብሆን አለቅም:: የሚለቀቅ ከሆነ ደግሞ ያ መብት ለሁሉም ሰው መጽናት አለበት:: ለኤርትራ የተሰጠ መብት ለሌላ የማይሰጥበት ምን ምክንያት አለ? ኦሮሞም አማራም ትግሬም በዚህ አይነት መነጠል ነበረበት:: ወደፈለገበት መቀላቀል አለበት:: የማይገባ መብት ሰጡ፣ መልሶ ራሱን አቃጠለው:: ሕዝብን ፈጀ:: ይሄ ያለ አቅም ያለ ችሎታ የሚደረግ ነገር መልሶ አገርንና መንግስትን ሕዝቡን ይጎዳል:: አገር ማለት መንግስት ማለት ደግሞ ሕዝብ ነው:: ሕዝብ ያልፈለገው ነገር ደግሞ ዋጋ የለውም:: ነገ ወዳቂ ነው:: ለታሪክም አይበጅም::

ሩሕ:- በሥልጣን ላይ ካሉና በውጭም ከሚገኙ ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ የሜጫና ቱለማ ማህበር አባላት አሉ ይባላል:: እነዚህ አባላት ለማህበሩ ያደረጉት ድጋፍ አለ?

መልስ:- የማህበሩ አባል ነኝ ብለው የሚናገሩት የኦነግ ሰዎች በርካታ ናቸው:: ነገር ለማህበሩም ያደረጉት የለም:: ብዙዎቹ ውጭ ናቸው:: እዚህ ካሉት ውስጥ የማህበሩ አባል ነኝ የሚሉት ዶክተር ነጋሶ ናቸው:: ዶ/ር ነጋሶም ተማሪ ሳሉ የማህበሩ ተራ አባል ነበሩ እንጂ ለማህበሩ ይሄን ሰሩ አንልም:: ብዙም አናውቃቸውም:: አንድ ቀን ራሳቸው እኔ እኮ ተማሪ ቤት ሳለሁ ከጉታ ሰርኔሳ ጋር መጥቼ ተማሪ ቤት አባል ገብቼ ነበርኩ ብለው ነግረውኛል:: በሌላ ጊዜም በሬድዮ ሲናገሩ የማህበሩ ሊቀመንበር ታደሰ ብሩ ነበር ሲሉ ሰምቻለሁ:: ታደሰ ብሩ የቦርድ አባል እንጂ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆኖ አያውቅም:: ለምሳሌ በውጭ አገር የኦነግ አባላት ናቸው ተብለው ከሚጠሩት ውስጥ ባሮ ቱምሳ በጣም ተሳታፊ ነበር:: አልፎ አልፎ ሌሎች ተሳታፊዎች አሉ:: ብዙ ትግል የሚያደርጉ ተማሪዎችን ወደ ማህበሩ የሚያስገቡ ነበሩ:: ዶ/ር ነጋሶ እሱ ነው ያስገባኝ ብሎ የነገረኝ ጉታ ሰርኔሳ በደርግ ዘመን ለአዲስ አበባ ለመጀመሪያ ከንቲባነት ተመርጦ ሳለ መንገድ ላይ መኢሶን ተብሎ የተገደለ ነበረበት:: በማህበራችን ውስጥ ብዙ ሰዎች አውቃለሁ:: ዶ/ር ነጋሶን አላውቃቸውም:: ውጭ ካሉት አዲሱ ቶሎሳ ሌሎችም አልፎ አልፎ ጥሩ ተሳትፎ የነበራቸው አሉ:: ሌላ የማውቀው ዮሐንስ ለታ አሁን ሌንጮ ይባላል:: እነ ጋላሳ ስሜ ዮሐንስ በንቲ ነኝ ብሎኝ ነበር የነገረኝ:: እውነት ለመናገር አላውቀውም:: መኖር ብዙዎች የማህበሩ አባል ነበሩ::

ሩሕ:- ቀደም ሲል አንዳንድ የማህበራችሁ አባላት እየተያዙ የሚመሰረትባቸው ክስ ከኦነግ ጋር የተያያዘ ነው:: ማህበራችሁ ከኦነግ ጋርም ሆነ ከሌሎች የኦሮሞ ተቃዋሚዎች ጋር ግንኙነት አለው?

ኮ/ል ዓለሙ:- ከየትኛውም ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ጋር ግንኙነት የለውም:: ማህበራችን ራሱን ችሎ በራሱ አመራር የሚመራ ነው:: ከኦነግም ጋር ግንኙነት የለውም:: ማህበራችን የሚፈልገው የኦሮሞ ህዝብ በዴሞክራሲ መብቱ የሚመርጠውን ሰው ይዞ መከተል ነው:: በራሱ በአምባገነንነት በጉልበት የሚመጣውን ሰው ማህበሩ ሊደግፈው አይፈልግም:: በሕዝብ ተሳትፎ የተመረጠ ሰው ካለ እንቀበላለን እንደግፈዋለን:: ከዚህ ውጭ በጠመንጃ የሚመጣውን ግዴታችን ካልሆነ በስተቀር በሰላም አንደግፈውም::

ሩሕ:- የመጫና ቱለማ ማህበር የፌደራል ሥርዓትን ይደግፋል ብለዋል:: የፌደራል አከላለልን በጎሳ ወይስ በመልክዓ ምድር ይሁን ይላል?

ኮ/ል ዓለሙ:- አሁን የተመሰረተው ጎሳን መሰረት አድርጎ ነው:: ጎሳን መሰረት አድርጎ ከተቋቋመ በጎሳው መሄድ አለበት:: ደግሞ መልክዓምድርን መሰረት ካደረገ ተስማምቶ ማድረግ አለበት:: ማቀላቀልን እኮ የሚከለክለው የለም:: የሕዝብ ፍላጎት ነው:: ይሄ እኮ ገዢዎቹ አለያይተህ ግዛ በሚባለው መልክ የመጣ ነው እንጂ ሕዝቡ ተገናኝቶ የሚበጀውን መክሮ ከዚህ እዚህ ይሻለናል ቢባል እኮ ሱማሌንም፣ ኤርትራንም፣ ጅቡቲንም ማምጣት ይቻላል:: አስተዳደሩ ከተስማማና ሰው ሰላማዊ ከሆነ የሚያለያየን ነገር ሊኖር አይችልም:: እኩልነት አላገኘንም በሚል ነው ሰው በቂም ላይ ተመስርቶ ነው እንለያይ የሚለው:: የመብት እኩልነትን ካገኘ የማይተባበርበት ምክንያት የለም:: ማንም ሰው ጥሩ አስተዳደር ካገኘ ወደ አስተዳደሩ መመለሱ አይቀርም:: ጀርመን ተለያይቶ ዴሞክራትና ኮሚኒስት ተብሎ ለዘመናት ጎራ ለይቶ ነበር:: ኋላ ግን ተስማምተዋል:: አሁን ደግሞ ኮሪያ በመስማማት ላይ ነው:: እኛ ግን በመገነጣጠል ላይ ነው ያለነው:: አስተዳዳሪው በጉልበቱ የሚመካ ሳይሆን በሕዝብ ስልጣን የሚመካ ከሆነ አንድ መሆን የማንችልበት ምክንያት አይኖርም፤ አንድም ልንሆን እንችላለን:: እስከዛ ግን የሚሻለው የራስን በራስ ይዞ መኖር ነው::

ሩሕ:- ለዚህች አገር ምን አይነት አስተዳደር ዕድገት ያመጣል ይላሉ?

ኮ/ል ዓለሙ:- ማንም ሰው በእኩልነት መብቱ ተጠብቆ፣ የጉልበት ነገር ቀርቶ፣ በሥርዓት አብሮና ተጋግዞ ወገኑን ፈልጎ በአንድነት ቢተዳደር የበለጠ ጠቀሜታ እንዳለው በእኔ በኩል አምናለሁ:: ሕዝቡ ምን እንደሚያስብ አላውቅም:: ሕዝቡም ከዚህ ውጪ የሚያስብ አይመስለኝም:: ጥሩ አስተዳደር ጠፍቶ የባሪያ አስተዳደር ስለነበር ተንገፍግፎ ነው መነጠልን የሚፈልገው:: የጉልበት አስተዳደር፣ እኔ ብቻ አውቃለሁ ባይነት ከጠፋ፣ ሰው ሁሉ በችሎታና በመብቱ የሚተዳደር ከሆነ፣ ይሄ የተነቀለው እርስቱና አገሩ በሕግ ከተጠበቀለት ማነው አንድነትን የሚጠላ ማንም የሚጠላ የለም:: እኔም አልጠላም፤ ሌላውም ሰው አይጠላም:: ሁሉም ሰው አይጠላም:: ግን የሚገዙን ሰዎች አይወዱም:: የተስማማን ከሆነና መጣላት ከቀረ በእነሱ ላይ መምከር ስለሚያስከትል አይወዱም:: አምባገነን ገዢዎች እንጂ ሕዝብ አንድነትን አይጠላም:: እኔ እንደማየው አስተዳደሪዎቹ አንድነትን ነስተው ወዲያና ወዲህ አምታቶ በስልጣን ለመቆየት ካልሆነ በስተቀር ሕዘቡ ይሄንን ይጠላል ብዬ አላስብም:: እኔም በራሴ አልጠላም::

ሩሕ:- ለሕዝቡ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ሊገልፁልን ይችላሉ?

ኮ/ል ዓለሙ:- አለ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊ ሕዝብ ነው:: ይሄን ሰላማዊ ሕዝብ በማይረባ መንገድ ለያይቶና በታትኖ አንተ ኦሮሞ፣ አንተ አማራ፣ አንተ ምዕራብ፣ አንተ ደቡብ፣ አንተ ሰሜን... ነህ ከማለት ይልቅ ተባብሮና ተስማምቶ የሚበጀውን ሥርዓት አውጥቶ በፌደራልም ቢሆን መተዳደሪያውን መስርቶ በጋራ አብሮ የመኖር ሀሳብ እንዲኖራቸው:: እያንዳንዱ ባለሥልጣን በሚያደርጉት ሕገ-ወጥ ሥራ ተገኝና ሆነው አገራችንን አደጋ ላይ እንዳይጥሉ አደራ እላለሁ::